# የእንስሳት በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

## በድንበር ዘለል በሽታዎች ላይ ያተኮረ የመስክ ማንዋል

2ኛ ዕትም










t.me/BooksandYou

# የእንስሳት በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

# በድንበር ዘለል በሽታዎች ላይ ያተኮረ የመስክ ማንዋል

2ኛ ዕትም

t.me/BooksandYou

የተጠናቀቀው በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የድጋፍ ድርጅት /USAID/ የምስራቅ አፍሪካው ክፍለ አህጉር /በአፍሪካ ህብረት የእንስሳት ሀብት ቢሮ/ AU-IBAR/ USDA-FAS /
Standard Methods and Procedures in Animal Health (SMP-AH) ፕሮጀክት
ከጆርጂያ ዩኒቨርሲቲ ፓቶሎጂ ዲፓርትምንት
ጋር በመቀናጀት ነው።
አቴንስ, ጆርጂያ, አሜሪካ 30602-7388

**የቅጂ መብት © 2015**
**በዶ/ር ኮሪ ብራውን**

t.me/BooksandYou

ISBN:

የኮንግረስ ቤተ መፃሕፍት  መለያ ቁጥር፡ 2015959451

የዚህ ማንዋል ገጾችና ሽፋኑ በውሃ የማይበላሹና በቀላሉ እርጥበት ባለው ጨርቅ የሚፀዱ ናቸው። ገጾቹም እንዲደርቁ ከፀዱ በ=ላ ክፍት ሆነው መቆየት አለባቸው።

t.me/BooksandYou

## ምስጋና

ይህ የእንስሳት በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየትና በድንበር ዘለል በሽታዎች ላይ ያተኮረ የመስክ ማንዋል  የአማርኛና የትግርኛ ትርጉም በመkለ ዩኒቨርሰቲ እንሳሳ ሕክምና ኮሌጅ የተዘጋጀ ሲሆን ቴክኒካዊ ድገፉ ደግሞ  በዩኤስኤኣይዲ ለኤፍኤኦ-ኢክታድ ኢትዮጵያና ለግብርና እንሰሳ ሃበት ሚኒስቴር በተሰጠው ድጋፍ እንዲሁም ይህንን ማንዋል ለማሳተም የሚያሰፍልገው ወጪ በኣወሮፓ ሕብረት (አውሮፓ ዩንየን) በቆላማ አካባቢዎች ለሚኖሩ የእንሰሳት አርቢዎች  ለኤፍኤኦ ኢትዮጵያ ፕሮጀክት በተሰጠ ድጋፍ ጭምር  የተፃሓፈ ነው$

**ለቅጂ ይገባኛል ባዮች**

ይህ  ፅሁፍ በአወሮፓ ሕብረት (አውሮፓ ዩንየን) የገንዘብ ድጋፍ የታተመ ነው$  በዚህ የተገለፀው ሁሉ የአወሮፓ ሕብረት  (አውሮፓ ዩንየን) ኦፊሴላዊ ሓሳብ ሆኖ ሊወሰድ አይችልም$

# የእንስሳት በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸው መሠረት መለየት

# የመስክ ማኑዋል

አዘጋጅ
**ኮሪ ብራውን**

መግቢያው በኣንድሪው ክላርክ

**የእንግሊዘኛው ማኑዋል ዝግጅት ተሳታፊዎች**

| | |
|---|---|
| ጀምስ ዋባቻ | ፒተር ማይና ኢቶንዴካ |
| ራኩዌል ሬክ | ጌታቸው ጋሪ |
| ጆራም ምግዊራ | ጆሴፍ ሴሩጋ |
| ሊንዳ ሎጋን | ኢሳም ማጌድ |
| ፒተር ንጅዋ | ሞሃመድ ሁሴን ዓሊ |
| ሙሪታይ ምባቡ | ኢቫንስ ሙቱማ |
| ኣሉማ ኣመሪ | ደቪድ ዋዌሩ |
| ሞሃመድ ሁሴን ሞሃመድ | ገ/ሚካኤል ገ/ ጎጃም |
| ኖሊና ናንቲማ | ኣመሃ ሰብስቤ |
| ፅጌ ክፍለየሱስ | ተኩሮ ኣ. ኦኩማ |
| ኣማኑኤል ስዋይ | ኣብዲ መሃመድ ኢልሚ |
| ሚካኤል ዲዮኔ | ማህሙድ ሁሴን ጃብራ |



**ተርጓሚ ዎች**
**1.ዶ/ር ዕፃይ ከበደ 2.ዶ/ር ዮውሃንስ ተክሌ 3.ዶ/ር አብርሃ ብስራት**
>>>>>>
የግራፊክስ መግለጫ በኢስሞንድ ቾኬ

## የማንዋሉ ይዘትና ማውጫ

**መግቢያ** ........................................ 1

**በዚህ ማንዋል የሚፈልጉትን እንዴት ማግኘት ይችላሉ** ........................................ 3

**ስነ ሕይወታዊ ደህንነት፡** በቀላል ዘዴ ጤናማ እንስሳትን ለመለየት የሚያስችሉ አምስቱ ሕጎች ...... 4

**የዶሮ በሽታዎች**

1. አደገኛ የአዕዋፍ ጉንፋን በሽታ (HPAI) ........................................ 7
2. የዶሮ ፈንግል (NCD) ........................................ 16

**የዓሳማ በሽታዎች**

3. የአፍሪካ አሳማ ትኩሳት በሽታ (ASF) ........................................ 25

**የበግ" የፍየል" የቀንድና የጋማ ከብት በሽታዎች**

**(ሀ) ተቅማጥ የሚያስከትሉ**

4. የበጎችና ፍየሎች ደስታ መሰል በሽታ (PPR) ........................................ 32

**(ለ) የመተንፈሻ አካላት በሽታዎች**

5. ተላላፊ የዳልጋ ከብቶች የሳምባ በሽታ (CBPP) ........................................ 38
6. ተላላፊ የፍየሎች የሳምባ በሽታ (CCPP) ........................................ 43
7. የምስራቅ ዳርቻ ትኩሳት በሽታ (ECF) ........................................ 48
8. የልብ አቃፊ ውሃ መቋጠር በሽታ (Heart water) ........................................ 52
9. የአፍሪካ የፈረስ በሽታ (AHS) ........................................ 56

ተጨማሪ፡ የበግና ፍየል ደስታ መሰል በሽታ ........................................ 32

**(ሐ) የአፍና እግር የመቁሰል ምልክቶች**

10. አፍተግር በሽታ ........................................ 62

**(መ) የቆዳ በሽታ**

11. የበግና ፍየል ፈንጣጣ በሽታ ........ 69

12. የጉርብርብ በሽታ ........ 76

13. ዕንፍሪር ግመል (ካመል ፖክስ) ........ 80

**(ሰ)የውርጃ በሽታ**

14. የውርጃ በሽታ (ብሩሴሎሲሰ) ........ 83

15. የስምጥ ሸለቆ ትኩሳት በሽታ (RVF) ........ 90

**ትኩረት የሚገባቸዉ ነባር በሽታዎች**

16. አዝጋሚ የመተንፈሻ አካላት በሽታ (ክሮኒክ ሪስፓራቶርይ ዲዝዝ) ........ 96

17. በደሮዎች የካንሰርና የአካል መደንዘዝና ያለመንቀሳቀስ በሽታ (ማሬክስ ዲዝዝ) ........ 99

18. የደሮ በርሳ ዕጢ በሽታ (ኤንፌክሾስ ባርሳል ዲዝዝ) ........ 102

19. የደሮ የፈንጣጣ በሽታ(ፋዉል ፖክስ ዲዝዝ) ........ 105

20. የደሮ የተቅማጥ በሽታ (ኮክሲዶሲስ ዲዝዝ) ........ 108

21. የገንዲ በሽታ (ትሪፓኖሶሞሲሰ) ........ 110

22. የግመል አዝጋሚ የመንተፈሻ አካል በሽታ (ክሮኒክ ሪስፓራቶርይ ዲዚዝ ኮምፕሌአ) ........ 112

23. የግመል የዕከክ በሽታ (እስከቢስ) ........ 114

24. የውሻ ዕብደት በሽታ (ረቢስ) ........ 115

**<u>ያሰተውሉ</u> ! በዚህ ማንዋል ቀይ አራት ማዕዘን ምልክት የሚያመለክተው የሽታው አምጪ ትህዋሲያንን ቫይረስ፣ ባክቴሪያ ወይም ፕሮቶዞዋን ሊሆን ይችላል፡፡**



*t.me/BooksandYou*

## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

**መግቢያ**

በየትኛውም ዓለም ጤናማ የሆኑ እንስሳትና ህብረተሰብ ሲኖሩ ለቀጣይ ዕድገት ያለው ኢኮኖሚ የላቀ ድርሻ አላቸው፡፡

በምስራቅ አፍሪካ አገሮች የእንስሳት ሃብት ኢንዱስትሪ ለክፍለ አህጉሩ የኢኮኖሚ መሰረት ነው፡፡ በአርብቶና በአርሶ አደሩ ደረጃ የእንስሳት ሃብት ምርት ለምግብ ዋስትናና ለአነስተኛ ኢኮኖሚ በመሪነት ደረጃ ጠቃሚነት አለው፡፡ በአገር ደረጃ የእንስሳት ጤናን መጠበቅ  የእንስሳት ሃብትን የውጭ ንግድ ለማሳደግ ወሳኝ ድርሻ አለው፡፡

ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታዎች ትኩረት የተሰጠበት ምክንያት በኢኮኖሚ ላይ ከሚያደርሱት ከፍተኛ ጉዳት በተጨማሪ በጣም ተዛማችና ተላላፊ በመሆናቸው ነው፡፡ በሽታዎቹ  እንስሳትን ለህመምና ለሞት በመዳረግ ህብረተሰቡ ከእንስሳቱ የሚያገኙትን ምግብና የገቢ ምንጭ ያሳጡታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የእንስሳትን የውጭ ንግድ ማዕቀብን በማስከተል በአገር ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡

የተወሰኑ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታዎች ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉና ጉዳት የሚያደርሱ ናቸው፡፡

በዚህም ምክንያት የእንስሳት ጤና ጥበቃ አገልግሎት ድንበር ዘለል በሽታዎችን የመከታተልና የመቆጣጠር ስራ ይሰራል፡፡ እነዚህን በሽታዎች በመለየት በፍጥነት ማሳወቅ /ሪፖርት ማድረግ/ መንግስትና የእንስሳት አርቢዎች ተገቢዉን የቁጥጥር ስራ በመተግበር በሽታዎቹ ሳይዛመቱ ቀድሞ ለመከላከል ይጠቅማል፡፡ ይህም የማሕበረሰቡ ህይዎት እንዲሻሻል ያግዛል፡፡

በዚህ መጽሃፍ እነዚህ ድንበር ዘለል በሽታዎች ዘርዝረን ስናቀርብ በዋነኝነት ስዕላዊ መግለጫዎቻቸውን በመጠቀም ነው፡፡ በመሆኑም ከእንስሳት ጋር ግንኙነት ያላቸው ማህበረሰብ በሽታዎችን እንዲለዩና በሽታዎቹን እንዴት ሪፖርት እንደሚያደርጉና እንዲያውቁም ጭምር ነው፡፡

## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

ማህበረሰባችን በእንስሳት አያያዝና እርባታ ስራዎችና በሽታዎችን ጭምር የመለየት ሃገር በቀል ዕውቀት ያለዉ መሆኑን እንረዳለን። በተጨማሪም እንስሳት አርቢዎች" እንስሳት ጠባቂዎች" ነጋዴዎችና ገበሬዎች" የስጋ መርማሪዎችና ሌሎችም ኑሮአቸው ከእንስሳት ሃበት ጋር የተያያዘ በመሆኑ በሽታዎችን በመከታተል"በመለየትና መረጃ በማቅረብ ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው የታወቀ ነዉ።

ይህ ማኑዋል በሽታዎችን በቀላሉ በመለየትና በመግልፅ በቀላሉ በቅርብ ላለው የእንስሳት ጤና ባለሙያ እና በአገር ደረጃ ላለው ተቋም ሪፖርት መላክ እንዲቻል የሚያግዝ በመሆኑ እንድትጠቀሙበት እናሳስባለን። ድንበር ዘለል በሽታዎች አስቀድመው ከታወቁና ከተረጋገጡ በቀላሉና በአነስተኛ ወጪ መቆጣጠር የሚቻል በመሆኑ የእንስሳት አርቢዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል።

የዚህ ማኑዋል ዋና ዓላማ፡- ሁሉም በጋራ በመስራት ጉዳት የሚያደርሱ በሽታዎችን በተቻለ መጠን ለመለየትና ለመቆጣጠር እንዲቻል ነው።

## በዚህ ማኑዋል ውስጥ የሚፈልጉትን እንዴት ማግኘት ይችላሉ?

የታመሙ ወይም የሞቱ ዶሮዎች ሲያዩ **ማኑዋሉ ውስጥ ስለዶሮ** የሚገልጸውን ክፍል ይመልከቱ (………)

የታመሙ ወይም የሞቱ ዓሳማዎች ሲያዩ **ማኑዋሉ ዉስጥ ስለአሳማ** የሚገልጸውን ክፍል ይመልከቱ (አፍሪካን ስዋይን ፌቨር)

### በዚህ ማኑዋል ስለ ሌሎች እንስሳት ዓይነቶች – በግ፣ ፍየል፣ የቀንድ ከብት፣ የጋማ ከብት

ተቅማጥ ሲያዩ **በዚህ ማኑዋል የበግና ፍየል ደስታ መሰል በሽታን** (PPR) የሚገልጸውን ክፍል ይመልከቱ

የመተንፈሻ አካላት በሽታ ምልክቶች ሲያዩ **የበግና ፍየል ደስታ መሰል በሽታ ፣ የፍየሎች ተላላፊ የሳንባ በሽታ፣ የዳልጋ ከብቶች ተላላፊ የሳንባ በሽታ፣ የልብ አቃፊ ውሃ መቋጠር በሽታ፣ የምስራቅ ዳርቻ ትኩሳት የአፍሪካ ፈረሶች በሽታ** የሚገልጸውን ክፍል ይመልከቱ

የአፍና ወይም የእግር መቁሰል ሲያዩ የ**አፍተግር** (FMD) በሽታን የሚገልጸውን ክፍል ይመልከቱ

የቆዳ በሽታ ምልክቶች ሲያዩ **የበግና ፍየል ፈንጣጣ በሽታ፣ ጉርብርብ በሽታ**ን የሚገልጸውን ክፍል ይመልከቱ

በእንስሳት ላይ ውርጃ ሲያዩ የ**ስምጥ ሸለቆ ትኩሳትና የውርጃ በሽታን** የሚገልጸውን ክፍል ይመልከቱ

**ነባርና ትኩረት የሚገባቸዉ በሽታዎች -**

የገንዲና የውሻ ዕብደት በሽታዎችን ይመልከቱ

የአፍና አፍንጫ አካባቢ እከክ/አፈማዝ/ቂጥኝ/ ይመልከቱ

## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

### ሥነ-ህይወታዊ ደህንነት

ሥነ ህይወታዊ ደህንነት ማለት እንስሳቶችን በበሽታ እንዳይያዙ ለመከላከል የሚወሰዱ አስፈላጊ እርምጃዎች ናቸው፡፡ እነዚህ እርምጃዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚተገበሩና በማንኛውም ጊዜ ሊተገበሩ የሚገባቸው ስራዎች ናቸው፡፡

በዚህ ላይ ዋነኛው ጉዳይ በሽታን ከሚያስተላልፉ ነገሮች ማለትም ከሰው፣ ከእንስሳት፣ ከመገልገያ ቁሳቁሶች ግንኙነት እንዳይኖራቸው በማድረግ ከበሽታ መከላከል ነው፡፡ ይህም ከግንዛቤ ዕጥረት የተነሳ የመገልገያ ቁሳቁስ፣ ሰዎችና እንስሳት በበሽታ የተበከሉ መሆናቸው ስለማይታወቅ ነው፡፡

ለምሳሌ ያህል ሌላ የእንስሳት እርባታን ሊጎበኙ ሲሄዱ በጫማዎ የሌላ እንስሳት እበት ረግጠው ሲመለሱ ወደ ራስዎ እንስሳት በሽታ አምጪ ተህዋስያንን ይዘው ሊመጡ ይችላሉ፡፡ ይህ ለሁሉም ተመሳሳይ እውነታነት አለው፡፡

እንዲሁም አዲስ እንስሳትን ወደ መንጋ ሲቀላቅሉ አዲስ የገባው እንስሳ የተሸከመው በሽታ ባለመታወቁ የተነሳ ለበሽታ ሊያጋልጥ ስለሚችል ነው፡፡ በመሆኑም አዲሱ እንስሳ ወደ መንጋው ከመቀላቀሉ በፊት ለይተው በማቆየት ጤናማ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ፡፡

ስለዚህ ሁሉም የእንስሳት አርቢዎች ስለ ሥነ-ህይወት ደህንነት አጠባበቅ (Biosecurity) ሂደቶች ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሚቀጥሉትን አምስት ዋነኛ የሥነ ህይወት ደህንነት አጠባበቅ ሂደቶችን ይከተሉ፡-

- የታመመውን ከጤነኛ መለየት!
- የመጫሚያ ንጽህና መጠበቅ፣
- የማይታወቅ ሰው ወደ እንስሳቱ እንዲጠጋ አለማድረግና፣
- መገልገያ ቁሳቁሶችንና ተሽከርካሪዎችን ንጽህና ማረጋገጥ፡፡
- በማንኛውም የሥራ እንቅስቃሴ ከጤነኛ እንስሳት ጀምረው ወደ ታማሚው በመሄድ ሁልጊዜ ከላይ የተጠቀሱትን ህጎች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**The STOP-and-GO RULES for BIOSECURITY**
**አቁም- እና- እርምጃ ውሰድ ህጎች ለሥነ-ህይወታዊ ደህንነት**

If you follow the **STOP-and-GO RULES** for your animals, you will keep them healthy and **STOP** bad diseases from coming.
እነዚህ **አምስቱ የሥነ ህይወታዊ ህጎች** ሲተገበሩ የእንስሳትዎን ጤና በመጠበቅ ሌላ አደገኛ በሽታ እንዳይገባ ይከላከላሉ።

**S** eparate sick animals from healthy ones right away
ወዲያዉኑ በሽተኛ እንስሳትን ከጤነኛ እንስሳት **መለየት**
**T** ake off your foot wear & clean them after travelling
ከጉዞ በኋ ጫማዎን **ማውለቅና ማፅዳት**
**O** nly people you know should come near your animals
**የሚያውgቸው ጤነኛ ሰዎች ብቻ** ወደ እንስሳትዎ እንዲቀርቡ መፍቀድ
**P** rotect your tools, equipment, & trucks – If you lend them, clean them thoroughly when returned
የመገልገያ ቁሳቁሶች " ተሽከርካሪና ሌሎች ዕቃዎች በበሽታ **እንዳይበከሉ መከላከልና** የተዋሱትንና ያዋሱትን ዕቃ ሲመልሱም ሆነ ሲመለስ በሚገባ የፀዳ መሆኑን ማረጋገጥ።

- ❖ and❖
- ❖ በተጨማሪ ❖

**GO** from healthy animals and then to sick animals when you are attending to them as the sick animals may be shedding a disease which you could take to the healthy ones

**በማንኛውም ወቅት በእንስሳትዎ ላይ ክትትል ሲያደርጉ ከጤነኛ እንስሳት ወደ በሽተኛ እንስሳት መሄድ አለብዎት**። ይህም ከበሽተኛ እንስሳት ወደ ጤነኛ እንስሳት ሲሄዱ በሽታ ይዘው እየሄዱ መሆኑን ይረዱ።

# የዶሮ በሽታዎችን የምንመለከትበት ክፍል




## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

### 1. አደገኛ የአዕዋፍ ጉንፋን በሽታ (HPAI)

**◆ ድንበር ዘለል የእንስሳተ በሽታ ነዉ። ◆**


**የትኞቹ ይጠቃሉ?**

ዶሮዎች ይታመማሉ። ዳክዬ ደግሞ የበሽታውን አምጪ ቫይረስ ሊሸከሙ ይችላሉ ነገር ግን በበሽታዉ እይጠቁም።



**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?**


ቫይረሱ በዶሮ ኩስ ወይም በምራቅ ዉስጥ ስለሚኖር ወደ ሌሎች ዶሮዎች በዚሁ መንገድ በመተላለፋ ይታመማሉ$



**<u>ያሰተውሉ</u>! በዚህ ማንዋል ቀይ አራት ማዕዘን ምልክት የሚያመለክተው በሽታውን አምጪ ቫይረስ የተሸከሙትን የሚያሳይ ነዉ።**

## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

**በበሽታዉ የተጠቁ ዶሮዎች ፣ የሚበሩ ዳክዬዎች እንዲሁም ሌሎች አዕዋፋት በሽታዉን በቀላሉ ወደ ሌሎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ።**



## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

**ካጠቃላዩ እንስሳት በበሽታው ምን ያህሉ ሊጠቁ ይችላሉ?**

አብዛኞቹ አዕዋፋትና ዶሮዎች ይጠቃሉ።

ይሞቱ ይሆን?

ከተጠቁት ዶሮዎችና አዕዋፋት አብዛኞቹ ይሞታሉ።





በዶሮ ገበያ ዉስጥ ቫይረሱ በቀላሉ ከዶሮ ወደ ዶሮ ይተላለፋል። በሰው አማካኝነትም ከአንድ የደሮ እርባታ ወደ ሌላ፣ ከሰፈር ወደ ሰፈር፣ እንዲሁም በተበከሉ ቁሳቁሶች አማካኝነት ለምሳሌ በዶሮ ማጓጓዣ ሳጥን፣ በመጫሚያ፣ በልብስ፣ በእንቁላል መያዥያ ዕቃዎች፣ በመኖ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ሊዛመት ይችላል።



ማንኛውም ከተበከሉ ዶሮዎች ጋር ግንኙነት ያለው ዕቃ ቫይረሱ ሊኖርበት ስለሚችል ሁሉም የዶሮ መኖሪያዎች" መያ¸ዎች" መሳርያዎች" ጫማዎች" የመኪና ጎማዎች በሚገባ ማፅዳት በሽታው እንዳይዛመት ያደርጋል።


## የታመሙ ዶሮዎችና አዕዋፋት የሚያሳዩት ምልክት

አብዛኛዉን ጊዜ በሽታው መኖሩ የሚታወቀው በድንገት ብዙ ዶሮዎች ሲሞቱ ነው።


የዶሮ ኮክኔ እና ኩልኩልቱ አብጦና ሃምራዊ ቀለም ሆኖ ይታያል

በስተግራ፡ በዚህ በሽታ የታመመ ዶሮ ኮክኔው በከፊል ወደ ሰማያዊ መልክ ይቀየራል።

በቀኝ በኩል እንደሚታየዉ የጤናማ ዶሮዎች ኮክኔ ምንጊዜም ቀይ ሆኖ ይታያል



በበሽታዉ የተጠቃ ዶሮ ኮክኔዉ ሰማያዊ/ሃምራዊ  እና ኩልኩልቱ ያብጣል




…የቀጠለየአደገኛ የአእዋፍ የጉንፋን በሽታምልክቶች

በታችኛው የእግር ክፍልና ጣቶች አካባቢ ቀይ ጭረት ያለው በዉስጡ ደም የመፍሰስ ምልክት ያሳያል




በስጋ ዶሮ በጭንቅላት ቆዳ ስር ሰማያዊ ቀለም ለብሶ ይታያል (Cyanosis )



በበሽታዉ የተጠቃ አዉራ ዶሮ ኮክኔዉ ሰማያዊ/ ሃምራዊ ይሆናል



ጭንቅላቱ አካባቢ ያብጣል



## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት


**በበሽታዉ ለሞቱ ዶሮዎች የሚደረግ ጥንቃቄ!**


በሚቀጥሉት ገፆችበአደገኛ የአዕዋፍ ጉንፋን በሽታየሞቱዶሮዎችን ይመልከቱ

በበሽታ የተጠረጠሩ ዶሮዎችን ከፍተን በምናይበት ጊዜ ከላይ የተገለፁት ምልክቶች ከታዩቫይረሱ ሰውን ሊያጠቃስለሚችልከፍተኛ ጥንቃቄያሻል።

### በአደገኛ የአእዋፍ ጉንፋን በሽታ የሞቱዶሮዎች

በታችኛው የአንገታቸው ቆዳ ስር ውሃ ይጥሮ ሲታይ ዋነኛ የአደገኛ የአእዋፍ ጉንፋን በሽታ ምልክት ነው





በውስጠኛው የጭን ቆዳ ስር ውሃ
አዝሎ ይታያል



በሳምባ ውስጥ ደምና ውሃ
ይቋጥራል

**እባክዎን የዚህን  በሽታ ምልክቶች ሲያዩ በአቅራቢያዎ ለሚገኘዉ የእንስሳት ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**

## 2. የዶሮ ፈንግል/የዶሮ ቆልምም በሽታ (NCD)


**ድንበር ዘለል በሽታ ነዉ፡፡**

### የትኞቹ ይጠቃሉ?

አብዛኛቹ የወፍ ዝርያዎችና ዶሮዎች በፈንግል በሽታ ሊያዙ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም ዝርያዎች አይታመሙም፡፡


### በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?

በታመሙ ዶሮዎች ኩስና ምራቅ ውስጥ ቫይረሱ ይገኛል፡፡ የታመሙ ዶሮዎች ከሚገኙበት አካባቢ በብናኝ ኩስ በምራቅ፣ በዶሮ ቤት ሳጥን፣ በመጫሚያ በተለያዩ ቁሳቁሶች እንደ አካፋ በመሳሰሉት ወደ ጤናማ አካባቢ ሊዛመት ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ሌሎች አዕዋፋትና ዶሮዎች ይበከላሉ፡፡




## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

**የተበከሉ ወፎችና የመገልገያ ቁሳቁሶች ከጤነኛ ወፎች ጋር ግንኙነት ካላቸው የዶሮ ፈንግል በሽታን (NCD) ሊያስተላልፉ ይችላሉ።**



**ካሉት ዶሮዎች ምን ያህሉ ሊጠቁ ይችላሉ ?**

ሁሉም ወፎች ወይንም ዶሮዎች በማንኛውም መንገድ ከቫይረሱ ጋር ንክኪ ሲኖራቸው በበሽታው ይያዛሉ ወይም ደግሞ የቫይረሱ ተሸካሚ ይሆናሉ። በሽታው በፍጥነት የሚተላለፍና በከፍተኛ ሁኔታ የሚዛመት ነው።



**ይሞቱ ይሆን?**

ሁሉም ባይሆኑ አብዛኞቹ በበሽታው የተጠቁ ዶሮዎችና ወፎች ይሞታሉ።

**የታመሙ አዕዋፍና ዶሮዎች የሚያሳዩት ምልክቶች**


የታመሙ ዶሮዎች መብላት ያቆማሉ" ወድቀዉ መነሳት አይችሉም፣ እንቁላል መጣል ያቆማሉ" ተቅማጥም ሊኖር ይችላል፣ የተወሰኑትም አንገታቸው ይቆለምማሉ እንዲሁም ሽባ ሊሆኑ ይችላሉ።

በዚህ በሽታ የታመሙትን ስንመለከት የሚበዛው ምልክታቸው ከአደገኛ የወፎች ጉንፋን በሽታ ጋር የሚመሳሰል ሲሆን መለየት የሚቻለው በላቦራቶሪ ምርመራ ብቻ ነው።

## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

የታመሙ አዕዋፍና ዶሮዎች የሚያሳዩት ምልክቶች (የቀጠለ)

የዓይናቸው ሽፋን ያብጣል ቀልቶም ይታያል



ተቅማጥና  የተቆለመመ አንገት የሚታይባት በበሽታው የተዳከመች ዶሮ



## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

የፈዘዘች ዶሮ አዕን ከፍታ

ስትተነፍስ የሚያመለክት



የተሸመደመደች/ሽባ የሆነች
ሆኖም ግን ንቁ ዶሮ



## በዶሮ ፈንግል የሞቱ አዕዋፋትና ዶሮዎች የሚያሳዩት ምልክቶች

የአይን ሽፋን መድማት እንዲሁም

የኮክኔ ሰማያዊ ሆኖ መታየት




ያበጠና ነጫጭ ጠቃጠቆ ያሉበት ጣፊያ



…የቀጠለ  የፈንግል ቁሰሎች

በመጀመሪያው የዶሮ ትልቁ የአንጀት ክፍል (cecal tonsils) ደም ቋጥሮ ይታያል



በተከፈተ ትልቁ አንጀት ውስጥ ደም ቋጥሮ ሲታይ



…የቀጠለ  የፈንግል ቁሰሎች

በአንጀት የመጀመሪያ ክፍል የውስጥ

ግርግዳ ላይ ደም ቋጥሮ ሲታይ



በተወሰኑ የአንጀት ክፍሎች ደም ቋጥሮ ሲታይ



**እባክዎን የዚህን በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥምዎት በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ያሳውቁ።**

# የአሳማ በሽታዎችን የምንመለከትበት ክፍል




## 3. የአፍሪካ አሳማዎች ትኩሳት በሽታ (ASF)

◆ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ ነው። ◆

### የትኞቹ ይጠቃሉ?

ሁሉም አሳማዎች የዱሮችን ጨምሮ በአፍሪካ አሳማዎች ትኩሳት በሽታ ይጠቃሉ። ለማዳ አሳማዎች በበሽታዉ የሚታመሙ ሲሆን የዱር አሳማዎች እንደ ከርከሮ የመሰሉ ደግሞ ቫይረሱን የሚሸከሙ ቢሆንም ለራሳቸው ግን አይታመሙም።



### በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?

ቫይረሱ በእዳሪ፣ በምራቅና በደም ዉስጥ ስለሚገኝ ከነዚህ ጋር በሚደረግ ንክኪ ወደ ሌሎች ጤነኛ አሳማዎች ይተላለፋል። ከዚህ በተጨማሪ መዥገሮች ቫይረሱ ከሚገኝበት ከርከሮ ወደ ጤነኛ አሳማ ያስተላልፋሉ። የተበከለ ትርፍራፊ የአሳማ ስጋ ለጤነኛ አሳማዎች መመገብ የበሽታዉን ስርጭት ሊጨምረዉ ይችላል።

### ከአንድ መንጋ ምን ያህል እንሰሳት በበሽታ ሊጠቁ ይችላሉ?

በአብዛኛው የእንስሳት መንጋ አባላት በበሽታዉ ሊጠቁ ይችላሉ።

### ይሞቱ ይሆን?


የሚታየው የሞት መጠን በሰፊው ሊለያይ የሚችል ሲሆን ከጥቂት እስከ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ አሳማዎች ሊሞቱ ይችላሉ።

**የቫይረሱ መተላለፊያ መንገዶች :**

(ሀ) መዥገሮች  የቫይረሱ ተሸካሚ የሆኑ ከርከሮዎችን  ደም ሲመገቡ   የቫይረሱ ተሸካሚ  ይሆናሉ።

(ለ) ቫይረሱን የተሸከሙ መዥገሮች የአሳማን ደም ሲመገቡ ቫይረሱን ያስተላልፋሉ።

(ሐ) የተበከሉ አሳማዎች በእዳሪና በምራቅ አማካኝነት ወደ ሌሎች ጤነኛ የአሳማ መንጋ ቫይረሱን ያስተላልፋሉ።




**የታመሙ አሳማዎች የሚያሳዩት ምልክቶች**

ከፍተኛ ትኩሳት፣ የጆሯቸዉና የጅራታቸው ቆዳ ይቀላል፣

መብላት ያቆማሉ በአንድ ላይ ይሰባሰባሉ።







የጆሮ ጠርዝ ከጥቁር ቀይ ወደ ሰማያዊ ቀለም ተቀይሮ ሲታይ




## የአፍሪካ አሳማዎች ትኩሳት በሽታ በሞቱ አሳማዎች ላይ የሚታዩ ምልክቶች

ጣፊያው ሲታይ ከ 4-5 እጅ መጠኑ ጨምሮ/አብጦ/ ይታያል




የጤነኛ አሳማ ጣፊያ ሲታይ




**…የቀጠለ የአፍሪካ አሳማዎች ትኩሳት በሽታ በሞቱ አሳማዎች ላይ የሚታዩ ምልክቶች**


ጣፊያ ከመጠን በላይ ጨምሮና ተሰነጣጥቆ ሲታይ



በጣም ያበጠና የጠቆረ ቀይ ቀለም ያላቸው የአንጀትና የጉበት ዕጢዎች ሲታዩ




ትልቅና ቀለሙ የጠቆረ ቀይ የሆነ
የኩላሊት ዕጢ ሲታይ



**እባክዎን የዚህን በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥምዎት በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ያሳውቁ።**

# የበግ ፍየል የቀንድና የጋማ ከብት/ ፈረስ ግመል ክፍል



ተቅማጥ

የመተንፈስ ችግሮች

የአፍና እግር የቁስል ምልክቶች

የቆዳ በሽታዎች

የውርጃ በሽታ


(ሀ)ተmማጥ

## 4. የበግና ፍየል ደሰታ መሰል በሽታ (PPR)

ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ ነው።

**የትኞቹ ይጠቃሉ?**

በግና ፍየል




**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?**

በጠጥ/ ተቅማጥና በምራቃቸው ሊተላለፍ ይችላል።




**ከመንጋው ምን ያህል እንሰሳ ት በበሽታው ሊያዙ ይችላሉ?**




አብዛኛው ጊዜ የበግና ፍየል ግልገሎች በበሽታው ይጠቃሉ።


ተጋላጭ የሆኑ የበግና ፍየልመንጋ በአብዛኛው በበሽታው ይታመማሉ።



**ይሞቱ ይሆን?**

በአብዛኛው የተጠቁት እንስሳትሊሞቱይችላሉ። በተለይም በዕድሜ አነስተኛየሆኑእንስሳትተጋላጮች ናቸው። በዕድሜ የጠነከሩ እንስሳትም ቢሆንተደራቢ አጋላጭ ሁኔታዎች ሲኖሩ ለምሳሌ በጥገኞች ተዋሲያን፡ በመኖ እጥረት የመጠለያና መኖርያ አለመኖርና መጥፎ የአየረ ፀባይ ጨምሮ በሽታው እንዲባባስ ተፅዕኖ ሊያደርጉ ይችላሉ።








**የታመሙ እንስሳት(በበግና ፍየል ደስታ መሰል በሽታ)**

የበግና ፍየል ደስታ መሰል በሽታ(ፒፒኣር) ፈሳሽ ከአፍና አፍንጫ ይወጣል መጥፎ ሽታ ያለው ተቅማጥ ያስከትላል







ሌሎች የበጎችና ፍየሎች ደስታ መሰል በሽታ ምልክቶች



በአፍና አፍንጫ እንዲሁም በአይን አካባቢ ቅርፊት መታየት



በዓይን አካባቢ ቅርፊት መፈጠር

በአፍና በአፍንጫቸው አካባቢ ቅርፊት መፈጠር፣ የሚፈስ ነገር ጭምር ይታያል




## በሞቱ እንስሳትላይ የሚታዩ ምልክቶች

የአፍ ውስጥ ቁስለት

በአፋቸው ውስጥ በሚፈጠር ቁስለት ምክንያት መመገብ አይፈልጉም



ሳንባቸው ደም ያዝልና ለመተንፈስ ይቸገራሉ



…የቀጠለ የበግና ፍየል ደስታ መሰል በሽታ በሞቱ እንስሳትላይ የሚታዩ ምልክቶች

ይህ በበሽታው ምክንያት አስቀድሞ የሚታይ የሳንባ በሽታ (Pneumonia) ሲሆን ሳንባው በብዛትና ትናንሽ ጠንካራ እብጠቶች የተሸፈነ ይሆናል።



**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያዩበአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**



## (ለ) የመተንፈሻ አካላት

### 5. ተላላፊ የዳልጋ ከብቶች የሳንባ በሽታ (CBPP)

◆ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ ነው። ◆


**የትኞቹ ይጠቃሉ?**

ሁሉም የዳልጋ ከብት ዝሪያዎች ለበሽታው ተጋላጭ ናቸው።



**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል ?**

በሽታው ሊሰራጭ የሚችለው በምራቅ ወይም  በአፍንጫ ፍሳሽ ብቻ ነው። እንስሳቱ በይበልጥ ተቀራርበው በሚኖሩበት ጊዜ በበሽታው የመያዝ እድላቸው ሰፊ ነው።




### ከአንድ መንጋ ምን ያህል እንሰሳት በበሽታ ሊጠቁ ይችላሉ?

እንስሳት ተጠጋግተው በሚኖሩበት ጊዜ ብዙዎቹ በበሽታው ይጠቃሉ።

### ይሞቱ ይሆን?

አብዛኛዎቹ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ የአተነፋፈስ ችግር ያለባቸው እንስሳት ይሞታሉ።



### የታመሙ እንስሳት የሚያሳዩት ምልክቶች

እንስሳት ይፈዛሉ፤ ከአፍንጫቸውም ቀጭን ፈሳሽ ይወርዳል።



## በተላላፊ የዳልጋ ከብቶች የታመሙ እንስሳት የሚያሳዩት ምልክቶች የቀጠለ



ከላም አፍንጫ ቀጭን ፈሳሽ ሲወርድ የሚያሳይ




አንገታቸው ወደ ፊት በመዘርጋት መተንፈስ
ሰ የስቸግራቸውና ሰ ስሉ ይታየሉ




እንስሳቶች በሽታው (CBPP) ሲያዙ አብዛኛው ጊዜ ይፈዛሉ፤ ከመንጋቸውም ይለያሉ።

## በበሽታው (CBPP) የሞቱ እንስሳት በድን ላይ የሚታዩ ምልክቶች

ሳንባው ቢጫ ሽፋን ይኖረዋል



ሳንባው በቢጫ ነገር ሊሸፈን ይችላል።




## በበሽታው (CBPP) የሞቱ እንስሳት በድን ላይ የሚታዩ ምልክቶች … የቀጠለ

በሳንባ ውስጥ ብዛት ያለው ቢጫ ነገር ይታይበታል




የተጠቃው የሳንባ ክፍል ሲቆረጥ ሻካራ ድምፅ ያለው ሲሆን ቅርፁም የእምነበረድ መልክ ይኖረዋል።




**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥሞዎት በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳት ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**

## 6. ተላላፊ የፍየሎች የሳንባ በሽታ (CCPP)

◆ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ ነው። ◆


**የትኞቹ ይጠቃሉ?**

ፍየሎች አና በአብዛኛው ከፍየሎች ጋር የሚዉሉ በጎች በሽታው ሊይዛቸው ይችላል።




**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል ?**

በምራቅ ወይም ደግሞ ከአፍንጫ በሚወጣ ፈሻሽ በሽታው ይተላለፋል ። ተቀራርበው የሚገኙ እንስሳት ለበሽታው ተጋላጭ ናቸው።



**ከአንድ መንጋ ምን ያህል እንሰሳት በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ?**




**ይሞቱ ይሆን?**

በአብዛኛው በበሽታው የተያዙ እንስሳት ይሞታሉ።



**የታመሙ ፍየሎች የሚያሳዩት ምልክቶች**

የታመሙት ፍየሎች ከፍተኛ የሰውነት ሙቀት፤ ለመተንፈስ መቸገር፤ ሳል፤ አቅም ማጣት፤ ክብደት መቀነስ፤ ማቃሰት፣ ከፍተኛ መጠነ ሞት፤ እንዲሁም ለመሞት ሲቃረቡ ከአፍንጫቸው አረፋማ ፈሳሽ ሲወጣ ይታያል።



**.... የቀጠለ የታመሙ ፍየሎች የሚያሳዩት ምልክቶች**

በበሽታው በተጠቁ ፍየሎች ከአፍንጫቸው ፈሳሽ/ንፍጥ ሲወርድ ይታያል



በበሽታው የተጠቁ ፍየሎች የመተንፈስ ችግር ይታይባቸዋል



## በበሽታ የሞቱ ፍየሎች ላይ የሚታይ ምልክቶች




የጠነከረ፤ ያበጠ እና በደም የተሞላ ሳንባ




በአብዛኛው ጊዜ ሳንባው ከውስጥ ሰውነት ጋር ሊጣበቅ ይችላል

በአብዛኛው ጊዜ በዚህ በሽታ የተጠቃ ሳንባ መሆኑን ለመለየት ያስችግራል



**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥሞዎት  በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳት ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**






## 7. የምስራቅ ዳርቻ ትኩሳት (ECF)


◆ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ ነው። ◆

**የትኞቹ ይጠቃሉ?**

ከብቶችና ጎሽ







**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል ?**

በበሽታው የተበከለ ቡናማ የጆሮ መዥገር ሲሆን የሚመርጠውና የሚመገበው ጆሮ ላይ በመሆን ነው።

**ከመንጋዉ ምን ያህል እንሰሳት በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ?**

በበሽታው ሊጠቁ የሚችሉ እንስሳት ብዛት የሚወሰነው በተበከሉ የመዥገሮች ቁጥርና በምንጠቀመው የመዥገር መድሃኒት የመከላከል አቅማቸዉ ላይ የተመረኮዘ ነው። ስርጭቱ ከጥቂት ወደ ብዙ እንስሳቶች ሊሆን ይችላል።


**ይሞቱ ይሆን?**

በበሽታዉ የተያዙ አብዛኛዎቹ እንስሳቶች ሊሞቱ ይችላሉ።



**የታመሙ ከብቶችና ጎሾች የሚያሳዩት ምልክት**

በበሽታዉ የታመሙ እንስሳት ከፍተኛ ሙቀትና
የዕጢ ዕብጠት ይታይባቸዋል።
መብላት ያቆማሉ ለመተነፈስ ይቸገራሉ ብሎም
ሊሞቱ ይችላሉ።





**የታመሙ እንስሳቶች (ECF) የሚያሳዩተ ምልክቶች**

የታመሙት እንስሳቶች ዕጢያቸው ያብጣል።




የመተንፈስ ችግር ስላለባት አፏን ከፍታ ትተነፍሳለች።



## በበሽታው (ECF) በሞቱ እንስሳት በድን ላይ የሚታዩ ምልክቶች

የታመመው እንስሳት ታርደው ሲታዩ ዕጢዎቻቸው አብጦ ይታያል።



ሳንባቸው ውሃ ጥሮና ክብደት ጨምሮ ይታያል።



**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያዩ በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**

## 8. የልብ አቃፊ ዉሃ መቋጠር በሽታ (Heart Water)

◆ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ ነው። ◆


### የትኞቹ ይታመማሉ?

የቀንድ ከብት፤ በግና ፍየል ይያዛሉ



### በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?


የልብ አቃፊ ውሃ መቋጠር (ሄርትወተር) መነሻው ባክተርያ በሚመስል ተህዋስ ሲሆን በመዥገር ይተላለፋል።



### ከመንጋው ምን ያህሉ እንሰሳት በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ?


በበሽታው የሚጠቁ እንስሳት ቁጥር የሚወሰነው በበሽታው የተበከሉ የመዥገር ብዛት፤ ቀድሞ የተጋለጡ እንሰሳትና የመዥገር መድሃኒት የመከላከል አቅም የሚዉሰን ነው። አንድ ወይም ብዙ እንስሳቶች ሊጠቁ ይችላሉ።

**የልብ አቃፊ ውሃ መቋጠር (ሄርትዋተር) ከአንድ እንስሳት ወደ ሌላ እንስሳት ሊተላለፍ የሚችለው በመዥገር ብቻ ነው፡፡**



**የታመሙ እንስሳት ምን ምልክት ያሳያሉ ?**

ከፍተኛ ሙቀት ይኖራቸዋል። ይፈዛሉ ቶሎ ቶሎ ይተነፍሳሉ። በመቀጠል የነርቭ ሙዛባት ምልክቶች ለምሳሌ ያህል ወድቀው መወራጨት እና የአንገት መቆልመም ያመጣል። ከዚያም ይሞታሉ።




**ይሞቱ ይሆን?**

በበሽታው የተጠቁ እንስሳት የመሞት እድላቸው ከፍተኛ ነው።

## በልብ አቃፊ የውሃ መቋጠር የታመሙ እንስሳት (ሄርትዋተር)

ወርቃማ ሽፋን መዥገሮች
በኮርማ ቆዳ ላይ ይታያሉ።



ደም መጠው ያበጡ ወርቃማ
መዥገሮች በቆዳ
ይታያሉ ።




## በበሽታው ታመው የሞቱ እንስሳት የውስጥ አካላት የሚታዩ ምልክቶች (ሄርትዋተር)

የልብ አቃፊ ውስጥ ብዙ ፈሳሽ ይgጥራል።



በሳንባ ውስጥና አካባቢው
ብዙ ፈሳሽ gጥሮ ይገኛል።



**እባክዎን የዚህን በሽታ ምልክቶች ሲያዩ በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳት ጤና ባለሙያ  ያሳውቁ።**


## 9. የአፍሪካ ፈረሶች በሽታ (AHS)

◆ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ ነው። ◆

### የትኞቹ ይጠቃሉ?


በአብዛኛው በበሽታው ፈረሶች የሚጠቁ ሲሆን በመጠኑ በቅሎዎችን ያጠቃል። አህዮችና የሜዳ አህያዎች በበሽታው አይጠቁም።





### በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?

ቫይረሱ በተናካሽ ነፍሳት ይተላለፋል።
ነፍሳቶች ከበሽተኛው ፈረሶች ወደ ጤነኞች በሽታውን ያስተላል




እነዚህ ነፍሳት በአብዛኛው የሚንቀሳቀሱት
ፀሃይ ስትወጣና ስትገባ ነው።
ነፍሳቱ ከ 1-4ሚ.ሜ. ቁመት
ያላቸውና በጣም ቀጭኖችም ናቸው።

## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

**የበሽታው አስተላላፊ ተናካሽ ዝንቦች ያላጠዉ የቁመት መጠን**

**የተናካሽ ዝንቦች ቁመት እከ 1 ሚ/ሜ እስከ 4 ሚ/ሜ ይደርሳል**





**ይዚህ ተናካሽ ዝንብ ቁመት 1ሚ/ሜ ይደርሳ**

**ይዚህ ተናካሽ ዝንብ ቁመት 4 ሚ/ሜ ይደርሳል**

### ከአንድ መንጋ ምን ያህል እንሰሳት በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ?

የሚታመሙት እንስሳት ብዛት የሚወሰነው በተበከሉ ነፍሳት መጠን ነው። ብዙ የተበከሉ ነፍሳት ካሉ ብዙ ፈረሶች ሊሞቱ ይችላሉ።


### ይሞቱ ይሆን?

መጠነ ሞቱ በፈረሶች ከፈተኛ ሲሆን በበቅሎዎች ላይ ዝቅተኛ ነው ።




## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

**በሽታው ከአንደ ፈረስ ወደ ሌሎች ፈረሶች የሚተላለፈው በትናንሽ በራሪ ነፍሳት ነው።**



### በበሽታ የተያዙ ፈረሶች የሚያሳዩት ምልክቶች


ከፍተኛ ሙቀት፤ ላብ፤ ሳል፤ ከፍተኛ የአተነፋፈስ ችግር፤ አፍንፍጫ አረፋ መድፈቅ በመቀጠልም ሞት ይከተላል።



የአይን ዉስጥ ሽፋን
መቅላትና ማበጥ።



ከዓይናቸው በላይ ባለው ቦታ
ዕብጠት ይታያል።



## የሞቱ ፈረሶች ላይ ለሚታዩ ምልክቶች

በአፍንጫው አረፋ ደፍቆ የሞተ ፈረ

ይታያል




በፈሳሽ የተሞላ ሳንባ ይታያል



## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

….የቀጠለ በበሽታው የሞቱ ፈረሶች ላይ ለሚታዩ ምልክቶች

የልብ አቃፊ በፈሳሽ ተሞልቶ የሚያሳይ።



**እባክዎን የዚህን በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥሞዎት በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**





## (ሐ) የአፍና እግር ቁስሎች

### 10. የአፍተግር በሽታ (FMD)

◆ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ ነው። ◆


**የትኞቹ ይጠቃሉ?**

ሸኮና ክፍት እንስሳቶች ሁሉ በበሽታ ይጠቃሉ። ከበጎችና ፍየሎች ይልቅ በሽታው የሚጠናው በዳልጋ ከብቶች ላይ ነው።



**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?**


የታመሙ እንስሳቶች በሚተነፍሱበት ወቅት ሌሎች ጤነኛ እንስሳቶች ከዚህ አከባቢ አየር ሲወስዱ በሽታው ሊተላለፍ ይችላል። ሌላኛው መላለፊያ መንገድ በተበከለ መኖና ውሃ ነው። በተጨማሪም ከሌሎች ከሰውነት ክፍሎች በሚወጡ ፈሳሾች መለትም እንድ ሽንት ወተት እዳሪና በአባላዘር ይተላለፋል።



## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት


### ከአንድ መንጋ ምን ያህል እንሰሳት በበሽታ ሊጠቁ ይችላሉ?

በአጭር ጊዜና በአፋጣኝ ሁኔታ በሽታው በመንጋ ዉስጥ ሊስፋፋ ይችላል። በሽታዉ **በጣም ተላላፊም** ነው። በመሆኑም አብዣኛቹ የተጠቁ እንስሳቶች የበሽታውን ምልክት ያሳያሉ ።



### ይሞቱ ይሆን?


አብዛኛው ጊዜ በሽታው ገዳይ አይደለም። በዕድሜ ትልቅ የሆኑ የታመሙ እንስሳት ከበሽታ የሚድኑ ሲሆን ጥጆችና አዲስ የተወለዱት ሊሞቱ ይችላሉ። በሽታዉ ባገገሙ ዉስን እንስሳት ላይ በእግራቸዉ ዘላቂ ችግር ሊያስከትልባቸዉ ይችላል።




(በተጨማሪም በሚቀጥለው ገፅ ያለውን ፎቶ ይመልከቱ)

**የታመሙ እንስሳቶች የሚያሳዩት ምልክት**

እግራቸው የቆሰሉ እንስሳቶች በጉልበታቸው ተንበርክኮ ሲተኙ የሚያሳይ (በአሳማ)



ከአፋቸዉ ምራቅ ሲዝረከረክ የሚያሳይ



.... የቀጠለ የአፍተግር በሽታ ምልክቶች

በላሟ አፍ የሚታየው ቁስል ውሃን በመቋጠር የጀመረ ነው።



በምርመራ ጊዜ የሚታይ የአፍ ድድ መቁሰል



…የቀጠለ የአፍተግር በሽታመምልክቶች

መዳን የጀመረ የአፍተግር በሽታ ቁስል




በሽኮና አካባቢዎች
የሚታዩ ቁስሎች በጣም አደገኛ ሊሆኑ
የሚችሉና የውጩ የሸኮና አካል
ተነጥሎ ሊወድቅ ይላል።



…የቀጠለ የአፍተግር በሽታ ምልክቶች

በአሳማዎች አፍንጫ ውሃ የመቋጠር እንዲሁም በሸኮናቸዉ መቁሰል ይታያል።



በእግር ላይ የሚታየዉ ቁስል በከፍተኛ ደረጃ የሚያሳቃያቸው ሲሆን ሁሉጊዜም ችግር ሆኖ ይቀጥላል።



....የቀጠለ የአፍተግር በሽታ ምልክቶች

በበጎች ምላስ ዉሃ
መቋጠር ይታያል።



**ውሃ መቋጠር በአፍታ እግር በሽታ ቀድሞ የሚታይ ምልክት በመሆኑ ይህን ምልክት የሚታይበት እንስሳ ሲያጋጥሞት በአፋጣኝ ከመንጋዉ ለይተው ሊያቀምጡ ይገባል።**

**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥሞት በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**

## (መ) የቆዳ በሽታ

### 11. የበግና ፍየል ፈንጣጣ በሽታ (SGP)

**◆ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ ነው። ◆**



### የትኞቹ ይጠቃሉ?

በሽታው በሁሉም የዕድሜ ክልል የሚገኙትን

ለማዳና የዱር የፍየልና በግ ዝርያዎችን ያጠቃል።

የቫይረሱ ዝርያ የተለያየ በመሆኑ የፍየል ፈንጣጣ ፍየልን የሚያጠቃ ሲሆን የበግ ፈንጣጣ ደግሞ በግን ያጠቃል።



### በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?

የቆዳ ቁስልና ምራቅ

በሽታውን ያስተላልፋሉ።


የደረቀ የቆዳ ቅርፊት ለረዥም ጊዜ ቫይረሱን

ሊያስተላልፍ ይችላል። ሌሎች ጤነኛ እንስሳት

ከዚሀ ከደረቀው ቁስል ጋር ከተነካኩ ሊታመሙ ይችላሉ።

በበግ ፈንጣጣ የተያዘ በግ ለሌሎች ጤነኛ በጎች ያስተላልፋል፡፡

እንዲሁም በፍየል ፈንጣጣ የተያዘ ፍየል ለሌሎች ጤነኛ ፍየሎች ያስተላልፋል።






**የበግና ፍየል የፈንጣጣ በሽታ/SGP/ የመተላለፊያ መንገድ**


**ሀ.** የታመመ እንስሳት ሆኖ የደረቀ የቁስል ቅርፊት ምልክት ያለው ወይም ደግሞ በእንጨት አጥር ምክንያት በቆዳው ላይ ጭረት ሲኖር ህይወት ያላቸው ቫይረሶች በአጥሩ በተቀረፈው ቁስል ሊተላለፍ ይችላል።

**ለ.** በመሆኑም ጤነኛ እንስሳት በተበከለው አጥር ሲተሻሹ በሽታው ይተላለፋል።




**ከአንድ መንጋ ምን ያህል እንሰሳት በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ ?**

በአብዛኛው ጊዜ  በመንጋው የሚገኙ እንስሳት በበሽታው ሊጠቁ ይችላሉ።



**ይሞቱ ይሆን?**

የተወሰኑ እንስሳት ሊሞቱ እንደሚችሉ ሆኖ በተጨማሪም በሌሎች ተፅዕኖ ፈጣሪ ምክንያቶች ማለትም በጥገኛ በሽታዎች በቂና የተመጣጠነ መኖ አለመኖርና በአየር ለዉጥም  ሞት ሊባባስ  ይችላል።



**በበሽታው የታመሙ እንስሳቶች የሚያሳዩት ምልክቶች**

አበጥ አበጥ ያሉ ጥቁር ቦታዎች
በበግ ፈንጣጣ የታመሙ
እንስሳቶች ላይ በከንፈራቸው አካባቢ ይታ




ራሰ ጥቁር የሆኑ በጎች (ዋንኬ ዝርያዎች)

በገላጭ በሆነ የፈንጣጣ ቁስሎች ተጠቅተው ሲታ



….የቀጠለ የበጎችና ፍየሎች ፈንጣጣ ምልክቶች

የበግ ፈንጣጣ
በቆዳቸው ይታያል።



ብዙ ያበጡ ቦታዎች
በመላው የቆዳ ክፍል ሊታዩ ይችላሉ።



## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

….የቀጠለ የበጎችና ፍየሎች ፈንጣጣ ምልክቶች

በግልፅ የሚታይ የፍየል ፈንጣጣ ምልክት



ከጅራታቸው በታች ቀይ ያበጡና በተለያዩ ቦታዎች የሚታዩ ሲሆን የበግ ፈንጣጣ መሆኑን ያሰረዳል።



በበግና ፈየል ፈንጣጣ የተያዙ እንስሳት በሳንባቸው የተለያዩና በብዛት የዕብጠት ቦታዎች ሊታዩ ይችላሉ።



**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥሞዎት በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**

## 12. የጉርብርብ በሽታ (LSD)

◆ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ ነው። ◆

**የትኞቹ ይጠቃሉ?**


የዳልጋ ከብቶች




**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?**

ሁለት የመተላለፍያ መንገዶች አሉ:

(1) በትንኝ፤ በሌሎች ተናካሽና ደም መጣጭ ዝንቦች




(2) የታመሙ እንስሳት ከጤነኞች እንስሳት ጋር ንክኪ በሚያረጉበት ወቅት በሽታው ሊተላለፍ ይችላል



## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት


### ከመንጋ ምን ያህል እንሰሳት በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ ?


በአብዛኛው ጊዜ በአንደ መንጋ ያሉት እንስሳት በበሽታው ይያዛሉ። በሽታው ሲጀምር ከፍተኛ የሰውነት ሙቀትና ትላልቅ እብጠቶች
በሁሉም የቆዳ ክፍሎች ይታያል።



### ይሞቱ ይሆን?

ጥቂት እንስሳት ሊሞቱ ይችላሉ።
የታመሙት እንስሳት ቆዳ ከጥቅም ወጭ ይሆናል።





## የታመሙ እንስሳት ላይ የሚታዩ ምልክቶች


በመላው ቆዳ ላይ ጎላ ጎላ ያሉ አብጠቶች ይታያሉ ።




እንዚህ በተለያዩ በታዎች ያሉ ወፋፍራም ዕብጠቶች ቆዳው ይበላሹታል።



…የቀጠለ የጉርብርብ በሽታ ምልክቶች



በቆዳ ላይ ብዙ ዕብጠቶች ሊታዩ ይችላ



በሽታው የሚያስከትለው ቁስለት በጣም ጥልቀት ያለው ነው

በበሽታው ምክንያት ከፍተኛ የቆዳ ላይ ጉዳቶች ይታያሉ።



**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥሞዎት በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳት ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**

## 13. ዕንፍሪር ግመል (ካመል ፖክስ)

◆ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ ነው። ◆


**መኒአን ይሓማ?**

ኣግማል የጥቀዕ ።




**ብኸመይ እቲ ሕማም ይሕዘን?**

ምሰቲ ቁስሊ ንክክእ ዘለዎ መሳርሒ ኣቑሑት"ክዳን "መግሃጫ በታ" ሰብን ዝሓመመ ግመልን ብንክክእ ናብ ጡዑይ ግመል የመሓላልፉ።




**ካብተን ዘለዋ ኣግማል ክንደይ ዝኣኽላ ተለኺፈን ይኾና?**

ኣብ ሓደ ደንበ ዝርከባ እንስሳት ሙብዛሕተአን ክልከፉ ይኽእላ።



**ይሞታዶ?**


ዝበዝሕ ግዘ ሞት ዝዋሓደ እዩ ። ኣብ ገላግል ሞት ካብ 40-50 ምእታዊ ኮይኑ ምኽንያቱውን ትሑት ኣታሓሕዛን ራሕዲ ዘለዎ ሙከት ኣየር እንትህሊ እዩ ።



**ዝሓመማ ኣግማል (ዕንፍሪር ግመል)**

ኣብ ኸንፈር ኣፍንጫ ክሳድን ከባቢ ዝሓበጡ ዝነkፁን

ዝፈስስ ደምን ቑስል ይራኣይ።





**እዞም ኣብ ላዕሊ ዝተገለፁ ምልክታት ኣብ ከባቢኹም እንትትሪኡ በይዛኹም ኣብ ቀረባ ንዘሎ ባዓል ሙያ ሓለዋ ጥዕና እንስሳ የፍልጡ።**


## (ሰ) የውርጃ በሽታ

### 14. የውርጃ በሽታ (ብሩሴሎሲሰ)

**ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ ነው።**

**የትኞቹ ይጠቃሉ?**

ብዙ የእንስሳት ዝርያዎች። ሰዉም በዚህ በሽታ ሊያዝ ይችላል።



**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?**

- ከበሽተኛ እንስሳት ከአካሎቻቸው ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ማድረግና ከውስጣቸው ከሚወጣ ፈሳሽ
- በዘህ በሽታ ከታመሙ እንስሳት ወተት በመጠጣት
- ከታመሙ እንስሳት በሚወጣ ፈሳሽ የተበከለ መኖ ወይም ውሃ ሲጠቀሙ
- በበሽታው የታመሙ እንስሳት በሚያስወርዱበት/ በሚወልዱት ጊዜ ከብልት ከሚወጣው ፈሳሽ ከተበከለ አካባቢ ጋር ንክኪ ሲፈጠር እንዲሁም የእንግዴ ልጅና የጨነገፈ ጽንስ በመነካካት ይተላለፋል።
- በሽታው ከአንድ መንጋ ወደ ሌላ የሚተላለፈው በታመመ እንስሳት ወይም ለበሽታው በተጋለጠ እንስሳት ሊሆን ይችላል

**ሰውን ከውርጃ በሽታ ለመከላከል መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች፡**

1. በዚህ በሽታ አምጪ ተህዋስያን የተበከለ ስጋ ሳይቀቀል አለመብላት።

2. ያልፈላ ወተት ወይም ደግሞ በፋብርካ ያላለፉ የወተት ውጤቶች ለምሳሌ አይብ መጠቀም  አለመጠቀም።
3. እንስሳትን በምናዋልድበት ጊዜ ከፕላሰቲክ የተሰሩ የእጅ Òንቶችን መጠቀምና በ‰ላም እጅ በደንብ  በማሸት በውሃና ሳሙና መታጠብ ያስፈልጋል።

4. ሌሎች የተበከሉ ዕቃዎችና  የመዉለጃ  ስፍራዎች ማፅዳትና በኬሚካል ማጽዳት ተገቢ ነው።

## ከመንጋው ምን ያህሉ እንስሳት በበሽታው ሊያዙ ይችላሉ

ከመንጋው ውስጥ አብዛኛዎቹ በበሽታው ሊያዙ ይችላሉ ሆኖም የበሽታው ምልክት ላይታይባቸው ይችላል፡ ፡

## እንስሳቶቹ በበሽታው ሲታመሙ ምን የሚታይ ምልክት ይኖራቸዋል ?


በአብዛኛው በግልፅ የሚታዩ ምልክቶች ማስወረድና የወተት ምርት መቀነስ ናቸው። በበሽታው የተያዙ ብዕድሜያቸው ትልቅ የሆኑ እንስሳቶች ስንመለከታቸው ጤነኛ መስለው ሊታዩ ይችላሉ።

**በሽታው በተለያዩ መንገዶች ይተላለፋል። ለምሳሌ፡**


ሀ. በበሽታው ከተያዘ እንስሳ የተገኘን ወተት ሳያፈሉ መጠጣት


ለ. እንስሳት ፆታዊ ግንኙነት በሚያደርጉበት ወቅት

ሐ. የእንግዴ ልጅና ከማህጸን የሚወጣ ፈሳሽ በመነካካት



## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት





**ይሞቱ ይሆን?**

በማህፀን ያለዉ ጽንስ ሊሞት/ሊጨነግፍ ይችላል።



## በበሽታው የታመሙ እንስሳቶች የሚያሳዩት ምልክቶች

ውርጃና የእንግዴ ልጅ መቅረት የበሽታው ምልክቶች ናቸው።




## በውርጃ በሽታ የሞቱ እንስሳቶች ላይ  የሚታዩ ምልክቶች

በበሽታው ምክንያት የጨነገፈ
የግመል ጽንስ






በበሽተው ምክንያት የጨነገፈ  የበግ ጽንስ



በዳልጋ ከብት እንግዴ ልጅ በጣም የወፈሩ ቦታዎች የውርጃ በሽታ ዋነኛ ምልክት ነው።

……… ምልክቶች በውርጃ በሽታ ከሞቱ ብኋላ የሚታ ምልክቶች

ጤነኛ እንግዴ ልጅ



በውርጃ በሽታ
የተበከለ እንግዴ ልጅ -
ብዙ ብጫማ የወፈሩ
ቦታዎች ይታይበታል




**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥምዎ በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**

## 15.የሰምጥ ሸለቆ የትኩሳት በሽታ (RVF)

◆ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ ነው። ◆


### የትኞቹ ይጠቃሉ ?

ፍየሎች፤ በጎች፤ የዳልጋ ከብቶች ግመሎችና የሰው ልጆች




### በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል ?

ተናዳፊ ነፍሳት በበሽታው ከተበከሉ ብኋላ ከእንስሳት ወደ እንስሳት በሽታውን ያስተላልፋሉ። ሰዎች በሽታው የተበከለች በወባ ትንኝ ሲነከሱ ወይም ከተበከለ እንስሳት ደም ጋር ንኪኪ ሲኖራቸው በበሽታው ሊጠቁ ይችላሉ።




## ከመንጋ ምን ያህል እንሰሳት በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ ?

ከከባድ የዝናብ ወቅት በኃላ የወባ ትንኞች በብዛት ሰለሚራቡ የመንጋው አባላት በሙሉ በበሽው ሊጠቁ ይችላሉ፡፡



**ይሞቱ ይሆን?**

በእርግዝና ላ ያሉ እንስሳት ሁሉም ያጨነግፋሉ፡፡ አዲስ ለተወለዱ እንስሳትም ከ 10 እጅ እስከ 50 እጅ ይሞታሉ $ በዕድሜ የገፉ እንስሳት የታመሙ ላይመስሉ ይችላሉ ሆኖም ግን ቫይረሱ ተሸከሚ ናቸው $  በበሽታው የተበከሉ ትንኞች  እንስሳት  ወደ እንስሳ /ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡



**የታመሙት እንስሳቶች ምን ዓይነት ምልክት ሊታይባቸው ይችላል ?**

ወርጃ፤ የግልገሎችና ጥጆች  አነስተኛ ደካማ መሆን፤  የሰውነት ሙቀት መጨመር፤ ለስላሳና አሙለጭላጭ የስውነት ክፍሎች ብጫ መሆን፡፡

## በበሽታው የታመሙ እንስሳቶች የሚያሳዩት ምልክቶች

በበሽታው ምክንያት ቢጫ የሆነ የውስጥ የዓይን ሽፋን



በበሽታው የተያዘች ፍየል ስታስወርድ ትታያለች



.... የቀጠለ የበሽታዉ ምልክቶች

በበሽታው ተይዛ ያስወረደች ግመል



## በበሽታው የሞቱ እንስሳቶች ላይ የሚታዩ ለውጦች

ያበጠና መልኩን የቀየረ ጉበት



**ህብረተሰቡን ከበሽታው ለመከላከል መውሰድ ያለባቸው እርምጃዎች**

**1.** በበሽታው ከተያዙ እንስሳት ጋር ንክኪ የሚደረግ ከሆነ መከላከያ ልብሶች ማድረግ ያስፈልጋል።

**2.** በምትሰራበት በአከባቢ የሚያሰውርዱ እንስሳት ካሉ በትንኙ አማካኝነት በሽታው እንዳይተላለፍ ጥንቃቄ ማደረግ ይገባል።

**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥሞዎት በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳት ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**



## ትኩረት የሚገባቸው ነባር በሽታዎች










## 16. አዝጋሚ የመተንፈሻ አካላት በሽታ (ክሮኒክ ሪስፓራቶርይ ዲዝዝ)

**የትኞቹ ይጠቃሉ?**

ብዛት ያላቸው ደረዎች በአዝጋሚ የመተንፈሻ አካላት በሽታ ሊያዙ ይችላሉ ።


**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?**

በተጨማሪ በሽታዎችና የሚያባብሱ ሁኔታዎች የሚከሰት ሲሆን በሽታው የሚመጣውም በባክተርያ ነው። ባክተርያው በደሮ ቤት አካባቢ ለብዙ ጊዜ የመቆየት ችሎታ አለው። በሽታው የሚተላለፍባቸው መንገዶችም በተበከሉ ዶሮዎች፣ ሰዎች በሚሰሩዋቸው ስራዎች፣ በተለከፉ ለማዳ ያልሆኑ አዕወፎች፣ ትናንሽ ነፍሳቶችና በተበከሉ የመገልገያ ዕቃዎች ሊተላለፍ ይችላል። ቀጥለው ያሉትን ስዕሎች ይመልከቱ።



**ከአንድ መንጋ ምን ያህል ደሮዎች በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ ?**

ግማሽና ከግማሽ በላይ ሊያዙ ይችላሉ ።



**ይሞቱ ይሆን?**
ከታመሙት ጥቂት ደሮዎች (5 ካብ ሚእቲ) የሞሞት ዕድል አላቸው። ይህን እንጂ እንደ እድሚያቸውና ሌሎች ሁኔታዎች ሊወሰን ይችላል።

## የታመሙ ደሮዎች የሚያሳዩት ምልክቶች

የታመሙ ደሮዎች አይበሉም፣መንቀሳቀስ ይቀንሳሉ ፣ እንቁላል መጣልና (ከ10-15%) ዕድገታቸው ይቀንሳል፣የእንቁላል ጥራት ይቀንሳል፣ ተቅማጥ ይኖራቸዋል፣ የተወሰኑትአንገታቸውና ራሳቸው ያጥፋሉ፡ ያለ መንቀሳቀስና መደንዘዝ ሊታየ ይችላል። የአፍንጫቸው ክፍል ይቆስላል፣ ይሸታሉ፣ ከአፍንጫቸው ፈሳሽ ይፈሳል፣ ይስላሉ፣ ለመተንፈስ ይቸገራሉ ያልተለመደ ድምፅ ያሰማሉ፣ በጣም የተጎዱ መሬት ላይ ይወድቃሉ በተጨማሪም አፋቸው ከፍተው ሊነፍሱ ይችላሉ።

የዚህ በሽታ ምልክቶች ምስ ከ ሓይለኛ የወፍ ሳል ሊመሳሰል ይችላል፣ ይሁን እንጂ በሚታየው የቁስለ ዓይነት መለየት ይቻላል ። ስለዚህ የመጨረሻው ማረጋገጫ ሊሆን የሚችለው በላቦራቶርይ ምርመራ ማረጋገጥ ነው ።



ይህ ስዕል በአዝጋሚ የደሮ በሽታ የተጠቃ አውራ ዶሮ ያሳያል ። ዓይኑ ቀይና ቁስል አለው፣ ኮክኔው ነጭና ቁስለ ይኖረዋል፣ከአቧራ ጋር የተቀላቀለ ከአፍንጫ የሚወጣ ንፍጥ አፍንጫው ዘግቶት ይታያል ። / ይህ ስዕልና መግለጫው ከ*MERCK Veterianry Manual* የተገኘ ሆኖ Courtesy of North Carolina State Poultry Health Management/።



በአዝጋሚ የደሮ በሽታ የተጠቃች ቄብ ደሮ። ዓይኗ ቆስሏል አብጧል፣ አፍንጫዋ በንፋጥ ተዘግቷል። / ይህ ስዕልና መግለጫው ከ*the poultry site* የተገኘ ነው/።



በኣዝጋሚ የደሮ በሽታ የተጠቃ አውራ ደሮ ተከፍቶ ሲታይ። በመጨረሻ ያለው ውይም ደግሞ የአየር መተላለፍያ ክፍልፋይ አብጦና ጉም የለበሰ መስሎ ይታያል ። / ይህ ስዕልና መግለጫው ከ*MERCK Veterianry Manual* የተገኘ ነው *Courtesy of American Association of Avian Pathologists*/።

**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥምዎ በአቅራቢያዎ ለሚ ገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**

## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት


### 17.በደሮዎች የካንሰርና የአካል መደንዘዝና ያለመንቀሳቀስ በሽታ (ማሬክስ ዲዝዝ)

**የትኞቹ ይጠቃሉ?**

ብዛት ያላቸው ቁብና እንቁላል መጣል የጀመሩ እንዲሁም የስጋ ደሮዎች በካንሰርና የአካል መደንዘዝና ያለመንቀሳቀስ በሽታ ሊጠቁ ይችላሉ ። በሽታው ኣብ የ 3 ሰምንት ዕድሜ ጀምሮ የሚታይ ሆኖ በተለይም ከ2 እስከ 7 ወራት ዕድሜ ባላቸው ደሮዎች ከፍ ብሎ ያጠቃል ።

**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?**


በሽታው ክሚያባብሱ ሁኔታዎች ማለትም ዕድሜና የደሮ ዝርያ ፣ ከእናታቸው የሚያገኙት የመከላከያ አቅም፣ በሽታው የሚያመጣ የቫይረስ ዓይነት፣ ተደራቢ ሌሎች በሽታዎችና የሰውነታቸው በሽታን የመከላከል ደረጃ ሲደክም ጋር ተያይዞ የሚመጣ የቫይረስ በሽታ ነዉ ። በሽታው በተበከሉ ደሮዎች የሚተላለፍ ሲሆን ቫይረሱ በተፈጥሮው በደሮ ህዋስ የሚኖር፣ ከደሮ በሚረግፉ የደሮ ላባዎችና ፀጉር በቅርብ ባሉት የደሮ መኖርያዎች ይሁኑ ራቅ ወዳለ ቦታ በመሰራጨት በቀላሉ ሊጠቁ ወደሚችሉ ሌሎች ደ



ሎች ይመልከቱ ።

**ከአንድ መንጋ ምን ያህል ደሮዎች በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ ?**

ግማሽና ከግማሽ በላይ ሊበከሉ ይችላሉ ።



**ይሞቱ ይሆን?**


ከተበከሉት ደሮዎች እስከ 50 በመቶ የሞሞት ዕድል አላቸው። ይሁን እንጂ እንደ ዕድሚያቸው ልዩነትና በሌሎች ሁኔታዎች ይወሰናል።


### የታመሙ ደሮዎች የሚያሳዩት ምልክቶች

በሽታው በተለያዩ ደረጃዎች የሚገለፅ ሲሆን እግራቸው ክንፋቸውና ሌሎች አካላቸው ይደነዝዛል ኣይንቀሳቀስም፣ የዓይናቸው ቀለም መቀየርና ዓይናቸው ይጠፋል፣ ቁስልና ዕጢ የሚመስል የቆዳ ካንሰር ይታያል፣ የሆዳቸው ይዘትና ግዝፈት ይጨምራል፣ የታመሙት ደሮዎች መብላት ያቆማሉ ፣ መንቀሳቀስ ይቀንሳሉ፣ ተቅማጥ ይኖራል፣ የተወሰኑት አንገታቸውና ራሳቸው ያጥፋሉ። የውስጥ አካላቸው ሲመረመር የካንሰር ዕብጠቶች በተለያዩ የውስጥ አካላት ይታያል። ለበለጠ መረዳት ቀጥሎ ያለው ስእሎች መመልከት ያስፈልጋል ።




በካንሰር መደንዘዝና ያለመንቀሳቀስ የደሮ በሽታ የቄብ ደሮዎች ይታያሉ ። አካላታቸው ደንዝዞ ምንቀሳቀስ አይችሉም። የመጀመርያዋ የቀኝ አንዳዶቹም የግራ እግራቸው ሁለተኛዋም ሁለቱም እግሮችዋና የአንዳዶቹ የቀኝ ስለደነዘዘና ስለእማይንቀሳቀስ ደሮዎቹ በመሬት ተዘርግተዋል። / ይህ ስዕልና መግለጫው ከ*MERCK Veterianry Manual* የተገኘ ነው Courtesy of North Carolina State Poultry Health Management/።





## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

በካንሰር መደንዘዝና ያለመንቀሳቀስ የደሮ በሽታ የተጠቁ ደሮዎች። የመጀመርያዋ ስንመለከት አካላትዎ የሚቆጣጠረው ኤኸፓቲክ ተብሎ የሚጠራው ነርብና በላይኛው ቀስት የተመላከተው ነርብ ከታችኛው የተመላከተው ቀስት ነርብ ሲወዳደር በበሕታው ምክንያት በጣም አብጦና ቆስሎ ይገኛል ። ሁለተኛዋ ደሮ በቀለምና ቅርፅ መቀየር ምክንያት ዓይኗ ሙሉ በሙሉ ጠፍቶ ይታያል ። ሶስተኛዋ ደሮ ደግሞ በካንሰር በሽታ በመጠቃትዋ ምክንያት ቆዳዋ ቆስሎና አብጦ ይታያል ። / ይህ ስዕልና መግለጫው ከ*Manual of Poultry Disease, Chief edditr-Jeanne Brugère-Picoux & Jean-Pierre Vaillancourt* የተገኘ ነው/.



በካንሰር መደንዘዝና ያለመንቀሳቀስ የደሮ በሽታ የተጠቁ ደሮዎች። የመጀመርያውና ሁለተኛው ስዕሎች የሚያሳዩት በበሽታው የተጠቁ ጥቛቁር ጉበቶች ሆነው ግዝፈታቸው ከሚገባ በላይ ትልቅና በተከፋፈለው አካላት ደግሞ ጥቛቁር ጉበቶች ብትን ብለው ወደ ካንሰር የተለወጡ ይታያሉ፣ ያበጠና ነጭ መልክ ያለው ተፈጥራዊ ያለሆነ ለውጥ ይታይበታል። በሶስተኛው ስዕል ደግሞ ወደ ካንሰር የተለወጠና ጣፍያው አብጦና ነጫጭ ነጠብጣቦች በሁሉም የጠፈያው ክፍል ተሰራጭቶ ይታያል። ይህ ስዕልና መግለጫው ከ*Manual of Poultry Disease, Chief edditr-Jeanne Brugère-Picoux & Jean-Pierre Vaillancourt* ዝተረኽበ እዩ/.

**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥምዎ በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**


## 18.የደሮ በርሳ ዕጢ በሽታ (ኤንፌክሾስ ባርሳል ዲዝዝ)

**የትኞቹ ይጠቃሉ?**

የደሮ በርሳ ዕጢ በሽታ ከደሮዎች ዕድሜ ተያይዞ የሚታይ ሲሆን ትናንሽ ጫጩቶችና በማደግ ላይ የሚገኙ በከፍተኛ ደረጃ ያጠቃል። በሽታው ከ 3 ሳምንት ዕድሜ አካባቢ ጀምሮ የሚታይ ሆኖ ዕድሚያቸው ከ3-6 ሳምንታት በሚሆኑት ላይ በከፍተኛ ደረጃ ያጠቃል።


**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?**

በሽታው አባባሽ ከሆኑ ሁኔታዎች ማለትም የደሮ ዕድሜ ፣ ከእናት የሚገኝ የሰውነት የመከላከያ መጠንና የቫይረሱ የበሽታማምጣት ተፈጥራዊ ልዩነት ተያይዞ የሚታይና የሚመጣ በሽታ ነው ። በሽታው ብተለከፉ ደሮዎች የሚተላለፍ ሆኖ በተጨማሪ በኩሳቸው ወደ ደሮ ቤቶችና በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ራቅ ባሉ በታዎች ተሰራጭቶ በቀላሉ ሊጠቁ የሚችሉ ሌሎች ደሮዎች በንክኪ ይተላለፋል ። ቫይረሱ ከደሮዎች ሰውነት ወደ ውጭ ከወጣ በኋላ በሌሎች ሁኔታዎች ሳይሸነፍ ለረጅም ጊዜ ይቆያል ። ቀጥለው ያሉት ስዕሎ



**ከአንድ መንጋ ምን ያህል ደሮዎች በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ ?**

ግማሽና ከግማሽ በላይ ሊያዙ ይችላሉ ።



**ይሞቱ ይሆን?**
ከታመሙት ደሮዎች ውስጥ ወደ 50 ከመቶ እጅ የሞሞት ዕድል አላቸው። ይሁን እንጂ እንድ የዶሮዎቹ ዕድሜና የቫይረሱ ዓይነት ሊለያይ ይችላል።

## የታመሙ ደሮዎች የሚያሳዩት ምልክቶች

በሽታው በተለያዩ ደረጃዎች የሚገለፅ ሆኖ ኮይኑ የታመሙት ደሮዎች መብላት ያቆማሉ ፣ ይፈዛሉ፣ ፀጉራቸውና ክንፋቸው ይዘረጋል ይበታተናል፣ መንቀሳቀስ ይቀንሳሉ፣ አልፎ አልፎም ተቅማጥ ይታየባቸዋል፣ የተወሰኑት አንገታቸውና ራሳቸው ያጥፋሉ። ይውስጥ አካላታቸውም ሲመርመር የካንሰር ዕብጠቶች በተለያዩ ውስጣዊ አካላት ይታያል ። ለበለጠ መረጃ ቀጥለው ያሉት ስዕሎች መመልከት ያስፈልጋል። ቁስሎቹ በዓይን የሚታዩበት አካላት ባርሳ በተባለ ዕጢና የእግር ጡንቻ፣ በደረትና ሌሎች አካላት ሲታዩ ነው። በተለይም የባርሳ ዕጢ ያበጣል፣ ይሰ፣ ይቆስፋል፣ ብጫ ቀለም ይኖረዋል፣ ደም ስር ይፈርሳል ደም ይፈሳል። በተጨማሪ የተጠቁት ጡንቻዎች ደም ይለብሳሉ ይደማሉ።ለተጨማሪ መረጃ ቀጥለው የተቀመጡት ስዕሎች ይመልከቱ።



በበርሳ ዕጢ በሽታ የተጠቁ ጫጩቶች። ዓይናቸው ይሸፍናሉ፣ አፋቸውና ራሳቸው ወደ መሬት ይጎብጣል፣ ፀጉራቸው ተበታትኖ ፈዛዛ ሆነው ይታያሉ / ይህ ስዕልና መግለጫው ከ*Manual of Poultry Disease, Chief edditr-Jeanne Brugère-Picoux & Jean-Pierre Vaillancourt* የተወሰደ ነው/።



በበርሳ ዕጢ በሽታ የተጠቁ የጫጩቶች የውስጥ አካላት፡፡ የመጀመርያው ስዕል የሚያመላክተው ውስጣዊ አካል በርሳ የሚባለው ዕጢ ደም ለብሶና ደምቶ እንዲሁም አብጦና ቆስሎ ይታያል ፡፡ ሁለተኛው ስዕል ደግሞ የእግርና ደረት ጡነቻዎች በበሽታው ምክንያት ደም ለብሰውና ደምተው አብጠውና ቆሰሉለው ይታያሉ፡፡ / ይህ ስዕልና መግለጫው ከ*Manual of Poultry Disease, Chief edditr-Jeanne Brugère-Picoux & Jean-Pierre Vaillancourt* የተወሰደ ነው/፡፡

**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥምዎ በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ፡፡**


## 19.የደሮ የፈንጣጣ በሽታ(ፋወል ፖክስ ዲዝዝ)

**የትኞቹ ይጠቃሉ?**

የደሮ የፈንጣጣ በሽታ ለሁሉም የዕድሜ ክልል የሚያጠቃ ቫይረስ ነው።በዋነኝነት ፀጉርና ላባ የሌላቸው የደሮ አካለት የሚያጠቁና ተላላፊም ነው ።


**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?**

በሽታው ወይም ቫይረሱ ለረጅም ጊዜ በመነካካትና በመቀራረበ የሚተላለፍ ሆኖ በሽታው ሊባበስ የሚችለው በኣንደ ቦታና ሰፈር ብዙ ደሮዎች ሲኖሩ ነው ። በተጨማሪ የተላየ ዕድሜ ያላቸው ደሮዎች መንገድ በአንደ ቦታና ሰፈር ማሰቀመጥ አናዱ የበሽታው ማባባሻ መንገድ ነው ። ቫይረሱ ከደሮ አካል ወደ አከባቢ ከወጣ ብምንም ነገር ሳይጎዳ ለረጅም ጊዜ ይቆያል። ብተጨማሪ ቫይረሱ በተለያዩ ነገሮች ስለማይጠቃ ኣብ መሬት ላይ ከሚረግፍ ላባና ፀጉር ለረጅም ጊዜ የሚቆይና ከበሽታው ያልዳኑ ደሮዎች ደግሞ ቫየረሱ ተሸከሚ ሆነው ቫይረሱን ወደሰፈራቸው ስለሚያልፍ ሰፈራቸው"ጉዝጓዛቸው፣ መኖቸውና ውሃ በመበከል ያልታመሙ ደሮዎች በበሽታው ሊያዙ ይችላሉ ። ቀጥለው ያሉት ዕሎች ይመልከቱ ።



**ከአንድ መንጋ ምን ያህል ደሮዎች በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ ?**

ግማሽና ከግማሽ በላይ በበሽታው ሊያዙ ይችላሉ ።



## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

**ይሞቱ ይሆን?**

ከተበከሉት ደሮዎች ውስጥ አብዛኛው የበሽታው ተጠቂ ሲሆኑ የሞሞት ዕድላቸው ግን በጣም ትንሽ ነው። ሆኖም ግን በበሽታው  ውስጣዊ አካላታቸው ማለትም ኣካላት ሆዳቸውና አንጀታቸውና የመንተንፈሻ ቸካላታቸው ሲጠቃ የሚታይ የሞት መጠን ሊከሰት ይችላል ።

### በበሽታው የታመሙት የሚያሳዩት ምልክቶች

በሽታው የውጭና የውስጥ ተብሎ በሁለት የተከፈለ ሆኖ በቫይረሱ የተለከፉት ደሮዎች  ኮክኔቸው፣ ኩልኩልታቸው፣ አፋቸው፣ እግራቸው፣ ቂጣቸው፣ ዓይናቸውና ሌሎች በፀጉርና  ላባ ያለተሸፈነ አካላታቸው ክፍት የሆነና ወጣ ወጣ ቁስለ በግልፅ ይታይባቸዋል ።   ቁስሉ በአፋቸውና በዓይናቸው አከባቢ በሚወጣበት ጊዜ ደሮዎቹ በተገቢ መንገድ እንዳይመገቡና እንዳያዩ  ስለሚያደርጋቸው በራብ ሊሞቱ ይችላሉ ። ከ ቁስል በተጨማሪ ደሮዎቹ ፀጉና ላባ ያለማብቀል የዕንቁላል ምርት መቀነስ ያጋጥማል ። በየውስጥ አካል ቫየረስ የተጠቁ ደሮዎች ደግሞ  በግሮሮቸው ፣ የላይኛው የማሰተንፈሻ አካላታቸው  ቁስል ሲፈጥር የመትንፋስ ችግር ያጋጥማል፣ ከፍ ያለ የሞት  መጠን ያጋጥማል። ለተጨማሪ መረጃ ቀቀጥለው ያሉት ስዕሎች ይመልከቱ።



## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

በደሮ የፈንጣጠ በሽታ የተጠቁ የተለያዩ ደሮዎች። ኮክኔቸው፣ ዓይናቸው ፣ አፋቸው በቁስሊ ተጠቀቶና ተጎድቶ ይገኛል ። / ይህ ስዕልና መግለጫው ከ*Manual of Poultry Disease, Chief edditr-Jeanne Brugère-Picoux & Jean-Pierre Vaillancourt* የተወሰደ ነው /።

**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥምዎ በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**


## 20.የደሮ የተቅማጥ በሽታ (ኮክሲዶሲስ ዲዝዝ)

**የትኞቹ ይጠቃሉ?**

የደሮ የተቅማጥ በሽታ ከዕድሜ ጋር ተያይዞ የሚታይና ትናነሾችና በማደግ ላይ ያሉት ደሮዎች በከፍተኛ ደረጃ ያጠቃል። በሽታወ ከ 3 ሳመንታ ዕድሜ አካባቢ ባላቸው ደሮዎች ጀምሮ የሚታይ ሆኖ በተለይም ዕድሚያቸው ከ3-6 ሳምንታት ባደረጉ ደሮዎች ድርሆ በከፍተኛ ደረጃ ያጠቃል ።

**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?**

በሽታው በሚያበሱ ምክንያቶች የሚነሳ ሲሆን እነርሱም የደሮው ዕድሜ ፣ የሰፈራቸው ውይም አካባቢያቸው የመርጠብና የሙቀት ሁኔታ፣ የበሽታ አምጭዎች ብዛትና የአፈጣጠር ዓይነት ልዩነት ተያይዞ የሚታይ በሽታና በፕሮቶዝዋ የሚመጣ ነው። በሽታው ብዝተለከፉ ደሮዎች የሚተላለፍ ሆኖ ፕሮቶዝዋው በደሮ ኩስ አማካኝነት ደርሁ ወደ አካባቢ ወይም የደሮ መኖርያ ከተሰራጨ በኋላ ሌሎች ደሮዎችን በተበከለ መኖ፣ ውሃና ሌሎች በመመገብ ወይም በመጠጣት ይተላለፋል። በመሆኑም ከዶሮ ቤት አያያዝ ማጓጓዝና ሞ የመካላከል ስራ ተዛምዶ የሚመጣ በሽታ ነው። የበሽታው መነሻ ፕሮቶዝዋ ከዶሮ አካላት ውስጣ ... ላ ሌሎች ደሮዎችን በቀላ...



**ከአንድ መንጋ ምን ያህል ደሮዎች በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ ?**

ግማሽና ከግማሽ በላይ ሊያዙ ይችላሉ ።

**ይሞቱ ይሆን?**

ከተያዙት ደሮዎች ውስጥ እስከ 50 በመቶ አካባቢ የመሞት ዕድል ሊያጋጥም ይችላል። በተለይም ከ3 እስከ 6 ሳምንታት ዕድሜ ያላቸው በብዙ የበሽታው መነሻ ፕሮቶዝዋ ከተጠቁ ከፍተኛ ሞት ሊያጋጥም ይችላል ።


**የታመሙ ደሮዎች የሚያሳዩት ምልክቶች**

በሽታው በተለያዩ ደረጃዎች የሚገለፅ ሆኖ ዋናወ ምልክቱ ተቅማጥና ደም የተቀላቀለበትም ጭምር ነው። በተጨማሪ የታመሙት ደሮዎች መኖ መብላት ያቆማሉ ፣ ይፈዛሉ፣ ፀጉራቸውና ክንፋቸው ይዘረጋል፣

መንቀስቀስ ይቀንሳሉ፣ የተለያየ ቀለምና ዓይነት ያለው ተቅማጥ ያሳያሉ፣ የተወሰኑት አንገታቸውና ራሳቸው ያጎነብሳሉ። እንዲሁም ዕድገታቸውና የሚሰጡት ምርት ይቀሰል። ውስጥ አካላታቸው ሲመረመር ዕብጠት፣ መቁሰልና መድማት በተለያዩ ውስጣዊ አካሎቻቸውና አንጀታቸው ይታያል ። ለበለጠ መረጃ ቀጥሎ ያለው ስዕሎችን መመልከት ያሰፈለጋል። ዋናዎቹ በዓይንናችን የሚታዩት ቁስሎች ቁስለታት በአንጀታቸው የሚፈጠሩ ናቸው ። ስለሆነም አንጀታቸው ያብጣል ፣ ይቆስላል፣ ብጫ መልክ ይኖረዋል፣ የመቅላትና መድማት ይታያል። ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ ያሉትን ስዕሎች ይመልከቱ።



በደሮ የተቅማጥ በሽታ የተጠቁ ጫጩቶች ። ደም የተቀላቀለበት ተቅማጥ ያሳያሉ፣ ራሳቸው ወደ መሬት ያጎነብሳሉ፣ ፀጉረራቸው ተበታትኖና ፈዘው ይታያሉ ። /ይህ ስዕልና መግለጫው ከ*Manual of Poultry Disease, Chief edditr-Jeanne Brugère-Picoux & Jean-Pierre Vaillancourt* የተወሰደ ነው/።



በደሮ የተቅማጥ በሽታ የተጠቁ ጫጩት ። በበሽታው ምክንያት በተለያዩ የአንጀት አካላት ደም መስለውና ደምተው እንዲሁም ኣብጦና ቆስሎ ይታያል። /ይህ ስዕልና መግለጫው ከ*Manual of Poultry Disease, Chief edditr-Jeanne Brugère-Picoux & Jean-Pierre Vaillancourt* የተወሰደ ነው/።


**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥምዎ በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**

## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

### 21.የገንዲ በሽታ (ትሪፓኖሶሞሲሰ)

**የትኞቹ ይጠቃሉ?**

የዳልጋ ከብቶች፣ ፍየሎች፣ በጎች፣ ዓሳማዎች፣ የጋማ ከብቶች፣ ግመል




**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?**



በአብዛኛው በተበከለች የቆላ ዝንቦች ንክሻ የሚተላለፍ በሽታ ነው። ጥቂት የሆኑ የገንዲ ዓይነቶች በሌሎች ተናካሽ ዝንቦች ይተላለፋሉ። ሆኖም ግን የቆላ ዝንቦች ዋነኛ አስተላላፊዎች ነው።

**ከአንድ መንጋ ምን ያህል እንሰሳት በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ ?**

ብዙ እንስሳቶች ላይታመሙ ይችላሉ። የሚወሰነው የቆላ ዝንቦች መኖር አለመሩ ነው።



**ይሞቱ ይሆን?**

የታመሙት ቆየት ብለው ይሞታሉ ነገር ግን በበሽታው ታመው ለረጅም ጊዜ ሊቆዩ ይችላሉ።

**በገንዲ በሽታ የታመሙ እንስሳቶች የሚያሳዩት ምልክቶች**

እንስሳቶች ለረጅም ጊዜ ይታመማሉ ሰውነታቸውም በጣም ይከሳሉ::



**በገንዲ በሽታ የሞቱ እንስሳቶች ላይ የሚታዩ ምልክቶች**

ከፍተኛ ክብደት መቀነስ




**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥምዎ በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**

## 22.የግመል አዝጋሚ የመንተፈሻ አካል በሽታ (ክሮኒክ ሪስፓራቶርይ ዲዚዝ ኮምፕሌአ)

**የትኞቹ ይጠቃሉ?ብ**

ግመላቸ ይታመማሉ።




**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?**


በሽታው ሊነሳ የሚችለው በአባባሽ ምክነያቶ ሆኖ ማለትም እንደነ የከባቢያዊ ኣየር ለውጥ "ደካማ አያያዝ"ዝቅተኛ የጤና አጠባበቅና ደካማ የአመጋገብ ስርዓት ከሚጠቀሱተ ውስጥ ናቸው። በሽታው በፍንዳታ ደረጃ በብዛት የሚከሰትበት ወቅት በጋን ወደ ዝናብ ወቅት ሲቀየር ነው ። ወጨፎ ያለበት ቀዝቃዛ ዝናብ የበሽታው ፍንዳታ በከፍተኛ ደረጃ የሚያባብሱ ናቸው ። የመተላለፍያ መንገዱና ስርጭቱ የሚወሰነው በበሽታው ተፈጥራዊ ልዩነት ሆኖ እነርሱም የተለያዩ ቫይረሶች "ፋንገሶች"ባክተርያዎችና ጭገኛዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ብዙ ግመላች በአንድ ቦታ ኣብ ሓደ ቦታ/ ጋጣ መኖርና የንፅህና ጉድለቶች በሽታው በፍጥነት እንዲስፋፋ ሊያደርጉ ይችላሉ።

**ከአንድ መንጋ ምን ያህል ግመሎች በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ ?**

በአብዛኛው ጊዜ ግዘ ከአንድ መንጋ ጢቂቶች ይታመማሉ ።



**ይሞቱ ይሆን?**
ጥቂት ግመሎች ይሞታሉ።



**የታመሙ ግመሎች የሚያሳዩት ምልክቶች**
ለመዳን ብዙ ጊዜ ይወስድባቸዋል "ከ5-6 ወር እርጉዝ የሆኑ ግመሎች ውርጃ ያሳያሉ"ሳል ይስላሉ"ንፍጥ ከ አፍንጫቸው ይወጣል "ሲያስተነፍሱ ድምፅ ያሰማሉ"ክብደታቸው ይቀንሳሉ ይደከማሉ "መብላት ያቆማሉ "ያልተስተካከለ ቁመና ይኖራቸዋል"ዓይናቸው ያለቅሳል አከባቢውም ያብጣል። በአጠቃላይ ሲታይ ሊሰጠተ የሚገባ አገልግሎትና ምርትና መራባት ከጊዜ ጋር እየቀነሰ ይሄዳል ።



**የሞትች ግመል**




**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥምዎ በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**

## 23.የግመል የዕከክ በሽታ (እስከቢስ)


**የትኞቹ ይጠቃሉ?**

ሰዎችን ጨምሮ ሌሎች የእንሰሳት ዓይነቶችም የሚያጠቃ ሆኖ የበሽታው አንሺ ጥገኞች በተፈጥሮ የተለያዩ ሰለሆኑ መልዕልቲ እዚህ ላይ የግመሎችን ብቻ ትኩረት ተጥቶታል።




**በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?**

ግመሎች እርስበራሳቸው በአካል ሲጣበቁ ሆኖ  ይህም ውሃ ሲጠጡ" በማደርያ ጋጣቸው "ክክ ያላቸው የመጫኛ ዕቃዎች "ኮርቻና ጉዝዕዝ በመሳሰሉት ከተበከለ ግመል ወደ  ጤናማ  ይተላለፋል።



**ከአንድ መንጋ ምን ያህል ግመሎች በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ ?**

በአብዛኛው ጊዜ ከአንደ መንጋ መካከለኛ ቁጥር  ይታመማሉ ። ሆኖም ግን ደካማ  አያያዝና የከባቢ የአየር ለውጥ ሲኖር  የሚታመሙት ብዛት ሊጨምር ይችላል ።



**ይሞቱ ይሆን?**

ከታመሙ ከረጅም ጊዜ በኋላ ሊሞቱ ይችላሉ። እዚህም ቢሆን ደካማ አያያዝና የአከባቢ ኣየር ለውጥ ሲኖር የሚሞቱት ቁጥር ሊጨምረ ይችላል ።

**የታመሙ እንስሳቶች የሚያሳዩት ምልክቶች**

ግልገሎች"የደከሙና በዕድሜ ትላልቅ የሆኑት ብበይበልጥ ይጠቃሉ ። ጤናማም የሚጠቁ ሆነው የበሽታው ምልክት የሚታይበት በታ ግን በተወሰነ ሊሆን ይችላል። የሚታዩት ምልክቶችም በሽታው ሲጀምር በሃይለኛ የታገዘ ሆኖ ዉሃ ይቋጥርና በመቀጠል ፀጉራቸው በመምለጥ ዕርጥበትና ፍሳሽ ቆዳቸው ላየ ይታያል ። ይህም ቆየት ብሎ የደረቀ ቁስልና በተለያያ ቦታ ጉበ ጉብ/ አበጥ አበጥ ብሎ ይታያል"ሁሌም በመደጋገም ቆዳቸው ያካሉ ። በሚበዛው ጊዜ ግዘ የሚጠቁት የውጭ የቆዳ ክፍሎችም ራስ" ቂጣቸው አካባቢ የፆታ ብልታቸው አካባቢ ነው። ፀጉር የተመለጠበት አካባቢ እስከ 2 ሴሜ ስፋት ሊኖሮው ይችላል። የቆየ በሽታ ከሆነ ቁዳው ላይ ግራጫ/ አመዳማ መልክና የተጣጠፈ ወፍራምና የተመለጠ ሆኖ ይታያል ። ለማጠቃለል የታመሙ ግመሎች ሰውነታቸው ይቀንሳል " ወተት መስጠትና መዋለድ ይቀንሳሉ።




**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያጋጥምዎ በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**

## 24.የውሻ ዕብደት በሽታ (ረቢስ)

### የትኞቹ ይጠቃሉ?

ሁሉም አጥቢ እንስሳት በበሽታዉ ይያዛሉ። ወፎች አይዛቸውም። ከእንስሳት ወደ ሰዉ ይተላለፋል ሰዉም ሆነ እንስሳት በበሽታዉ ከተያዘ አይድንም።



### በሽታው እንዴት ሊይዛቸው ይችላል?

በሽተው በታመመ እንስሳት ንክሻ ይተላለፋል

በተለይም በውሻ ንክሻ አማካኝነት ይተላለፋል።

በተጨማሪ በምራቅ፣ በደም ወይም በቆሰለ የአካል ክፍል

ቫይረሱ ሊተላለፍ ይችላል።



# በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት




### የታመሙት እንስሳቶች የሚያሳዩት ምልክት ምን ይመስላል?

ምልክቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- ምራቅ ማዝረክረክ
- ቅፅበታዊ የሆነ የባህርይ ለውጥ
- የተረጋጉ እንስሳትና ስጋ በል እንስሳቶች ባህሪያቸው ቁጡ ይሆናሉ።
- የዱር እና ሳር በል እንስሳት የመፍዘዝ ምልክት ያሳያሉ
- የዱር እንስሳት ወደ ሰው ሊቀርቡና ዕደኛ ሲመስሉ ይታያሉ

### ከመንጋ ዉ ምን ያህል እንሰሳት በበሽታ ሊያዙ ይችላሉ ?

አልፎ አልፎ የሚታይ ቢሆንም ፍፁም ገዳይ በሽታ ነው።



**ይሞቱ ይሆን?**

በዉሻ ዕብደት በሽታ የታያዙ ሁሉም ይሞታሉ $ በዚህም መሰረት በሽታዉ ዝቅተኛ የመታመም እድል እና ከፍተኛ ሞት የሚያስከትል ብሎ መክፈል ይቻላል::

**በበሽታው የታመሙ እንስሳቶች**

በዕብድ ውሻ በሽታ ምክንያት፣

የፈዘዘችና የወደቀች ጥጃ



**በዉሻ ዕብደት በሽታ የሞቱ እንስሳቶች**

በበሽታዉ የሞቱ እንስሳት የሚያሳዩት ልዩ የዉስጣዊ አካል ምልክት የለም $

**እባክዎን የዚህ በሽታ ምልክቶች ሲያዩ በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳ ጤና ባለሙያ ያሳውቁ።**

## በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት



ሌሎች  በቦካ አሳታዎች ቡድን ድርጅት የተዘጋጁ ማንዋሎች

- የመስክ  ናሙና መሰበሰብ ማንዋል የእንስሳት በሽታዎችን መለያና ማፍጠኛ
- የእንስሳት ተላላፊ በሽታዎች ገላጭ ማንዋል
- የውጭ የእንስሳት በሽታዎች (ኡሳሃ) 7ኛ እትም
- የእርሻ ደህንነት :  የአሜሪካ የምግብና እርሻ መከላከል
- የእርሻ ሽብርን መከላከል - መሪ አጣቃሽ



# የእንስሳት በሽታዎችን በጥቅል ምልክቶቻቸዉ መሠረት መለየት

## በድንበር ዘለል በሽታዎች ላይ ያተኮረ የመስክ ማንዋል

2ኛአትም









AFRICAN UNION
INTERAFRICAN BUREAU FOR ANIMAL RESOURCES

USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

USDA

1785
The University of Georgia

ISBN